## የጤና መብት ሲባል ምን ማለት ነው?

የጤና መብት የሰዎችን ክብር እና ልዕልና መሠረት ያደረገ የሰው ልጆች መሠረታዊ መብት ነው:: ለዚሁ መብት እውቅና የሰጠው የመጀመሪያው አለምአቀፍ ስምምነት የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባሕላዊ መብቶች አለም አቀፍ ቃል ኪዳን ስምምነት ሲሆን ይኸው ስምምነት ስምምነቱን የፈረሙና የተቀበሉ መንግስታት ለጤና መብት እውቅና የመስጠትና ቀስ በቀስ መብቱ እንዲከበር የማድረግ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ያስቀምጣል:: በዚህ ሰነድ አንቀጽ 12 ንዑስ ቁጥር 2 ላይ ሲገኝ የሚችል ከፍተኛ የጤንነት ደረጃ ማግኘት የሚለውን በመተንተን

*"…. የጤና መብት ሲባል ሲገኝ የሚችል ከፍተኛ የጤንነት ደረጃ ለማግኘት አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ መገልገያዎች ፣ ቁሳቁስ፣ አገልግሎትና ምቹ ሁኔታዎችን የማግኘት መብት ነው"*

በማለት ገልጾታል::

መብቱ ከዚህ በተጨማሪ ለጤንነት መጠበቅ እና መሻሻል አስተዋጽኦ ሲያደርጉ የሚችሉ ነገሮችን የማግኘት ለምሳሌ ንፁህ የመጠጥ ውሃ እና የአካባቢ ንጽሕና፣ ንጽሕናውን የጠበቀ ምግብና የመኖሪያ ቤት አቅርቦት፣ ጤናማ የስራና የመኖሪያ አካባቢ ሁኔታ፣ የጤና እና የስነ ተዋልዶ ትምህርት እና ጤናን የሚመለከት መረጃ ማግኘትን የሚያካትት ሆኖ እናገኘዋለን::

## የመንግስት ግዴታዎች

የጤና መብት እንደ ሌሎቹ የሰብአዊ መብቶች በመንግስት ላይ ሶስት የተለያዩ ግዴታዎችን ይጥላል:: የጤና መብትን በተመለከተ መንግስታት ያለባቸውን ግዴታ በኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባሕላዊ መብቶች አንቀጽ 12 ንዑስ ቁጥር 2 ሥር እናገኘዋለን:: እነዚህም መብቶቹን ***የማክበር፣ የማስከበር*** እና ***የማሟላት*** ግዴታዎች ናቸው::

የጤናን መብት ***የማክበር*** በሚለው ግዴታ ስር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሰዎች በጤና መብታቸው ለመጠቀም ያላቸውን አቅም የሚያግዱ ወይም አሉታዊ ተጽእና የሚያሳድሩ እርምጃዎችን፣ ፖሊሲዎችን እና ሕጎችን ከማውጣት የመቆጠብ ግዴታ እንዳለበት የተቀመጠ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ መንግስት መብቱ በሀገሪቱ ካለበት ደረጃ እንዲያሽቆለቁል የሚያደርጉ ሕጎችና ፖሊሲዎችን ከማውጣት መቆጠብ ያለበት መሆኑን ያስቀምጣል:: ለምሳሌ ለሕክምና አገልግሎት የሚያስፈልግ ወጪን መንግስት በሚወስን ጊዜ በጣም ድሀ የሆኑት የኅብረተሰብ ክፍሎችን ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የማያደርግ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት::

***የማስከበር*** ግዴታ ስር መንግስት ጠቅላላውን ኅብረተሰብ በጤና መብት መገልገልን ከሚከለክሉ ሶስተኛ ወገኖች የመጠበቅ ግዴታ አለበት:: ይህ ማለት የግለሰቦች፣ የተለያዩ ቡድኖች እና አካላትን ተግባራት መቆጣጠር አለበት ማለት ነው:: በተለይም መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት በኅብረተሰቡ የጤና መብት ላይ ተጽእኖ እንዳያሳድሩ መንግስት አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን እርምጃዎች መውሰድ አለበት:: ለምሳሌ መንግስት የግሉ ሴክተር የከባቢ አየርን ከመበከልና የኅብረተሰቡን ጤንነት አደጋ ላይ እንዲወድቅ ከማድረግ እንዲቆጠብ የተለያዩ መመዘኛዎችንና ሕጎችን በማውጣት የኅብረተሰቡ ጤና እንዲጠበቅ ማድረግ አለበት::

***የማሟላት*** ግዴታ ሥር ደግሞ መንግስት አዎንታዊ የሆኑ እርምጃዎችን እንዲወስድ ይገደዳል:: ዜጎች በጤና መብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስፈላጊ የሆኑትን አገልግሎቶች የማቅረብ ግዴታ በመንግስት ላይ ተጥሏል:: ይህ ግዴታም ሕግ ማውጣትን፣ አስተዳደራዊ መዋቅርችን መዘርጋትን፣ በጀት መመደብን፣ የፍትሕ ስርዓቱን ማሻሻልን እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ሊጠይቅ ይችላል:: መንግሥት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወይም ለችግር የተጋለጡ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የጤና ፍላጐቶች ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የሚያደርጉ ልዩ እርምጃዎችም መውሰድ ይጠበቅበታል:: ለምሳሌ በተለይ ከፍ ብለው የተገለፁት የኅብረተሰብ ክፍሎች ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ከኤች አይ ቪ ጋር የሚኖሩ ግለሰቦችን የጤና መብት ለማሟላት እንዲቻል በቂ የሆነ ሀብት ለዚሁ አገልግሎት የመመደብ ግዴታ አለበት::

የማሟላት ግዴታ በሶስት ተከፍሎ እናገኘዋለን:: እነሱም ማፋጠን፣ ማቅረብ፣ እና ማራመድ /ማበረታታትና ማስተዋወቅ/ ናቸው:: ማፋጠን የሚለው መንግስት ግለሰቦች ወይም ማኅበረሰቦች የጤና መብታቸውን ለመጠቀም የሚያስችሉ ወይም እገዛ የሚያደርጉ

አፃንታዊ እርምጃዎች እንዲወሰድ የሚጠይቅ ሲሆን፣ ማቅረብ የሚለው ግለሰቦች ወይም ማኅበረሰቦች ከቁጥጥራቸው ውጪ በሆነ ምክንያት በራሳቸው የጤና መብታቸውን ለማሟላት በሚያዳግታቸው ጊዜ የጤና አገልግሎቶችን መንግስት እንዲያቀርብ ያስገድዳል:: ማራመድ በሚለው ስር ደግሞ ለጤና መብት አስፈላጊ የሆነ ሁኔታ እንዲፈጠር እንዲጠበቅ ወይም ወደ ቀድሞ ሁኔታው እንዲመለስ የተለያዩ እርምጃዎችን መንግስት መውሰድ አለበት የሚል ነው:: መብቱን ማራመድ መብቱ ሙሉ በሙሉ እውን




እንዲሆን አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች አንዱ መሆኑ ተገልጿል:: ጤናን የሚመለከቱ መረጃ ዎች በስፋት እንዲኖር ማድረግ በዚህ ግዴታ ሥር የሚወድቅ ነው::

ሀገራችን ኢትዮጵያም በአለም አቀፍ ደረጃ የተ ሟላ የጤና መብት እንዲኖር አካቶ የወጣውን የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባሕል መብቶች ቃል ኪዳን ያፀደቀች በመሆኑ መንግስትም በቃል ኪዳኑ ላይ የተቀመጡትን ግዴታዎች የመወጣት ኃላፊነት አለበት::

★★★

*ይህን አጭር ጽሁፍ ያዘጋጀው አክሽን የባለሙያዎች ማህበር ለህዝብ (አፕአፕ) ነው:: አፕአፕ በ1985 ዓ.ም የተቋቋመ አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን የተቋቋመበትም አላማ ህግና ሰብአዊ መብትን በመጠቀም የድሆችን በተለይ የሴቶችና የህጻናትን ሰብአዊ መብቶችን ማስከበር ነው::*

*ለበለጠ መረጃ ከታች በተቀመጠው አድራሻ ያነጋግሩን::*

ስድስት ኪሎ፣ ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል
በሚወስደው መንገድ ፤
ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤትን አለፍ ብሎ፣
አዲስ የተሰራው የቴሌኮሚዩኒኬሽን ህንፃ ፊት ለፊት
ፖ.ሣ.ቁ. 12484፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ 251-11-1-243555፣ፋክስ 251-11-1243558
ኢ-ሜይል፡apap@ethionet.et
ዌብ ሳይት(ድረ-ገፅ): **http:**\\www.apapeth.org

# *የጤና መብትና የመንግስት ግዴታዎች*

APAP

## አክሽን የባለሙያዎች ማህበር ለሕዝብ (አኘአኘ)